# የትኛው ነው ድሃ?

ሐረገወይን ስለሺ፤

ምን እያላችሁ ነው?
ጅምላ ይዛችኋል የደቦ ንግግር?
መዝገበ ቃላቱ መጽሐፉ ይውጣና ይሄ ቃል ይመርመር፤
ካልሆነም፤ ካልሆነም ትርጉሙ ዛሬውኑ ይቀየር!
የትኛው ነው ድሃ?
ገንዘብ ሃብት ንብረት፤
መኪና ቪላ ቤት፤
ቤሳ ቤስቲ የሌለው እንኳንስ አካውንት?
እሱማ———፤
ምግባሩ ሃ——ብ——ቱ——፤
ኑሮው ሸ———ል——ማ——ቱ፤
ሚዛን የጠበቀ ቁጣና ትዕግስቱ፤
ባህል ሃይማኖቱ፤
ኑሮው ሸልማቱ፤
ይሄማ—————???
ቢ———ሞ———ት——፤
ሞቱ ተ–ፈ–ጥ–ሮ–አ–ዊ!!!
ቢኖር፤
በስብእና፤
ከወግ ከማእረግ ጋር፤
በህሊናዊ ክብር፤
የአጸደ-ሥጋ እንግልቱ፤
ብሶቱ፤ እጦቱ፤ ኑሮው አለመሙላቱ?
ከጥንት የመጣ አዳማዊ፤
ሰው ሰራሽ ኢ–ፍትሃዊ፤
ይ—ሄ—ማ???
ድሃ ሊባል አይችልማ!

እኮ! የሃገሬ ባላገር ገበሬው?
የእግሩ ንቃቃት ሳንቲም የሚደብቀው?
ቅያሪ የሌላት እጀ ጠባብ ለብሶ፤
የጭቃ መደብ ላይ፤
ከምድጃው አጠገብ መሬት እፍ ብሎ፤
ቁርበትና ነቱን ወይም አጎዛውን፤
ሣርና ጭዱን ሲቻል ገለባውን፤
ጎዝጉዞ ነስንሶ፤
ኩበት ተንተርሶ፤
«ተመስገን አምላኬ» ብሎ የሚተኛው?
አጋር የሌለውን የቅርብ ጎረቤቱን፤

ረዳት የሌላቸው አዛውንት ሴቲቱን፤-
ሊረዳ አስቦ፤
ችግርን በዘዴ ሊከላ ወንፊልና ደቦ?
ሃገር ብትደፈር፤
ትንንሽ ልጆቹን፤
ነፍሰ ጡር ሚስቱን፤
ጧሪ አልባ እናት አባቱን—ጥሎ፤
በኵራት ወደ ግንባር ተመልምሎ፤
ጠላት ተናዳፊው፤
የሃገር ድንበር አስከባሪው?
እሱ ይሆን ድሃው?
ወይስ ተሸካሚው፤
እንጨት ፈላጩ፤ ዛፍ ቆራጩ?
ቅጠል ለቃሚ፤ ኮማሪዋ ነች ወይ ሸቃጩ፤
ኑሮው ከእጅ ወደአፍ ስለሆነ?
በሃይማኖቱ በምግባሩ ስለታመነ?
ከቶ ስሙ «ድሃ» ሆነ?
ድሃማ ይኸ አይደለም።
ድሃማ፤
በትርጉም እንስማማ፤
እና———፤
ኑ አብረን «ይሙት ብለን» እንርገመው!
ድሃማ ሃገር የሚሸጠው!
ባንዳው!
የሰው ደም መጣጩ፤ ነው!!!
የሕዝብ ብሶት የማይሰማው፤
በጉልበቱ፤ በሙያው በትምህርት በእውቀቱ?
ሳይሆን በምላሱ፤
ተመግቦ ለራሱ፤
ቀማኛው፤ ጉቦኛው፤ በሥልጣን ዋልጌ ዘማው!!!
በሕዝብ ገንዘብ በሃገር ሃብት ተምሮ፤
በእኔነቱ ሰንሰለት በሆዱ ብቻ ታስሮ፤
የሕዝብን ዋይታ፤ ሰቆቃ፤ የሕዝብን ብሶት፤
የሚለካ በደሞዙ በሃብቱ ማነስና መብዛት፤
ሃገር ታሪክ የሚሸጥ፤
ስገዱለኝ የሚለው፤ አሱም ለባለሥልጣን አጎብዳጅ፤
ፍትህ አጉዳይ የበታቹን አሳዳጅ፤
ሆዱ ከብዶት ራሱ ቀሎት፤
ለራሱ ማደር እንቅልፍ ነስቶት፤
በሰብአዊነት መኖር የሚጠነው፤
ቅል ይመስል ባዶ ራስ የተሸከመው፤
ከመቃብር በላይ ስም የማይተርፈው፤

ታሪክ ስሙን የማይዘክረው፤
ድሃ ማለት ይህ ነው፤
ቀዳማዊ አዳማዊ ሞትን ቢሞት?———እንዴ ይሙታ ምን ይቆጫል?
ደሃራዊ ሲያል መውረድን?————ያድርግበት ብለነዋል!
ሣልሳዊ ከመቃብር በላይ ይሙት!———ይሁንበት ይገባዋል!
እሰይ ሞት አበጀህ!
ውሰደው ተመላልሰህ፤ ሃገር ሳያጠፉ ቶሎ ቶሎ አፋጥነህ!
በቃ ይሙት፤ ይሙታ!
ሃሳበ–ድሃ! ባህርየ—ድሃ! ምግባር—ድሃ! ብለነዋል፤
ከሰው ተራ አውጥተነው——— ድሃ ብለን ሰየምነው፤
በአንድ ድምጽ ይ——ሙ——ት አልነው።